**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

# የመምህር የኔሰው ሰማዕትነት የአቶ መለስ አገዛዝ ግፍና በደል ከልክ የማለፉ ነፀብራቅ ነው!!

*ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ድርጅታዊ መግለጫ!!*

በምዕራብ ኢትዮጵያ ዳውሮ ዞን ዋካ ከተማ ቤንዚን አርከፍክፎ ራሱን ያቃጠለው የመምህር የኔሰው ገብሬ ኅልፈት መላው የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ቤተሰቦችን ክፉኛ አስደንግጦናል። መምህር የኔሰው ግፍና በደል አንግሽግሾት በሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ፊት ለፊት ተቃውሞውን ከገለፀ በኋላ ራሱን በእሳት አቃጥሎ መሞቱ አሸብሮናል፤አሳዝኖናል።ኅልፈቱም በአቶ መለስ የሚመራው አገዛዝና ባለሥልጣናቱ በህዝብ ላይ እየፈፀሙት ያለው ጭቆና ከልክ ማለፉን የሚያንፀባርቅ ሆኖ አግኝተነዋል።

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያችን ሰው መኖር የማይችልባት አገር ሆናለች። አንዳንዶች ከአገር ሲሰደዱ፣ ሌሎች የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እያደረሰባቸውን ያለውን የመከራ ህይወት እየተጋፈጡ፣እንዲሁም ከስራ እየተፈናቀሉ ነገን እንኳን በተስፋ እንዳይመለከቱ የጨለመባቸው መሆኑ ለየኔሰው ገብሬ ልብ የሚሰብር አሟሟትና ሞት ምክንያት ሆኗል።

ከኢሳት ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ አበበ ገላው በመጀመሪያ ዜናውን እንደዘገበውና በተለያዩ የዜና አውታሮች (የአሜሪካ ድምጽ፣ ቢቢሲ፣ ወዘተ) እንደተገለጸው መምህር የኔሰው ገብሬ ለፍትሕ ይታገል የነበረ፣ በሙያው ትጉና ተወዳጅ ነበር፡፡ በስነ ምግባር የታነጸ፣ በሙያው የወደፊቱን ትውልድ የሚያንፅ ከመሆኑም በላይ፣ በትምህርቱ ጎበዝ፣ በተማሪዎቹ ዘንድ የሚከበር ውድ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ስንሰማ ደግሞ ሃዘናችን የበለጠ መራራ ሆኗል።

መምህር የኔሰው ገብሬ ከፍተኛ የህዝብ ፍቅር ያለው፣ ትሁትና በደልን አጥብቆ የሚጠላ፤ የአገዛዙ ባለስልጣናት የሚፈፅሙትን ህገ ወጥ ተግባራት አጥብቆ የሚያወግዝ፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በጥብቅ የሚቃወም፣ ፍትሕ ናፋቂ፣ በየስብሰባው ሐቅን የሚሰብክ ደፋር በመሆኑ ከዚህ በፊት ታስሮ እንደተፈታና በተቃውሞው ምክንያትም ከሚወደው ስራው እንዲባረር የተወሰነበት ዜጋ ነበር። በመሆኑም መምህር የኔሰው በሃገሪቱ እውነትና ፍትህ እንደሌለ፤ ነፃነትና ዴሞክራሲ በዚህ ሥርዓት በፍፁም የማይታሰቡ ነገሮች መሆናቸውን በመገንዘቡ ለነፃነት ትግሉ፣ ለሌሎች የነጻነት ታጋዮችና ለወጣቱ ትውልድ አርኣያ በመሆንና ለነፃነት እንዲነሳሱ በማሳሰብ ራሱን መስዋዕት ማድረጉን ስንሰማ ሐዘናችን እጥፍ ድርብ አድርጎታል።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ቤተሰቦች፣ የእያንዳችን ሕይወት ከፈጣሪ የተሰጠ ስጦታ ነው ብለን እናምናለን፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን የማንም ሰው ሕይወት መጥፋት የለበትም በሚል መርህ የሚመራ ሲሆን ማንኛውም ሰው በጎሣ፣ በመደብ፣ በርዕዮት-ዓለም፣ ወዘተ ሳይከፋፈል ሰብዓዊ መብቶቹ ተከብረለውለት ማየትን ይመኛል። ምክንያቱም አንድ ኢትዮጵያዊ ጉዳት ሁላችንንም ይጎዳልና!

መምህር የኔሰው ገብሬ የተለየ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ከእኛ አንዱና በስሙ የሚታወቅ ወንድማችን ነበር። ለኛ እንደማንኛውም የሰው ልጅ ወንድም፣ አጎት፣ የቅርብ ጓደኛ፣ መምህር ወይም የስራ ባልደረባ ነው። የሱ በዚች ሰዓት በሕይወት አለመኖር በሁላችንም ዘንድ ጥልቅ ሐዘን አንግሷል። ከሐዘናችን ጥልቀት የተነሳ ጸሎታችንና ንግግራችንን ወንድማችን የኔነሰው ብቻ ሆኗል። የኔሰው የመላው ፍትህ ናፋቂዎች ቤተሰብ አባል የነበረ ብቻ ሳይሆን አዲሲቷ ኢትዮጵያን ተመሥርታ ለማየት የሚመኝም ነበር፡፡

በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ምክንያት እየደረሰብን ያለው ስቆቃ፣ ግፍና ኢሰብዓዊ በደል የኔሰውን እንዳማረረው ሁሉ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንንም በተለያየ መልኩ በየፈርጁ መከራ

እያደረሰባቸው እንደሆነ የየዕለት ተሞክሯችን ነው፡፡ የኔሰው ነጻነት ለተራቡ ሕዝቦች አርኣያ በመሆን ራሱን መስዋዕት አድርጎ ፍትሕ ይመጣ ዘንድ የነጻነት ትግሉን ሲያቀጣጥለው ሌሎች ደግሞ ከዚህ በመያተናነስ መልኩ አፈና፣ እስራት፣ ግፍና ስቃይ አንገሽግሿቸው አገር ጥለው በመሰደድ ላይ ይገኛሉ። በስደት ጉዞ ለሞት ይዳርጋሉ፤ በመንገዳቸውም ላይ ይህ ነው ለማይባል እጅግ አሠቃቂ አደጋ ይጋለጣሉ፡፡ ግማሾቹም ያላቸውን ጥሪት ሁሉ አሟጥጠው ኑሮዋቸውን በተለያየ አገራት በማድረግ ፈጽሞ አዲስ የሆነ ሕይወት በማያውቁት ሕዝብና አገር እንዲመሩ ይገደዳሉ፡፡ አብዛኞቹ በድህነት ቀንበር ስር ያሉ እህቶቻችን የቤት ሰራተኛ ሆነው ለመቀጠር በሚሔዱባቸው የአረብ አገራት እጅግ ዘግናኝ የሆነ የጉልበት ብዝበዛ፣ አካልዊና ወሲባዊ ጥቃት ይፈፀምባቸዋል። በዚህም ምክንያት ለሞት የተጋለጡት እጅግ በርካታዎች ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሰቆቃ ከመጋፈጥ ይልቅ ስደትን የሚመርጡ ኢትዮጵያዊያን ቁጥራቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየበረከተ እየበረከተ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።

ወጣቱ ትውልድ ተስፋው ተሟጦ ኑሮውን መምራት አቅቶታል። በአገዛዙ ላይ ያለው እምነት አልቆ የመኖር ትርጉሙ ጠፍቶበት ተስፋ ቢስ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል። ህወሃት/ኢህአዴግ ግን የኢትዮጵያውያንን የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል ይልቅ ሙያ አድርጎ የያዘው ተግባር ስለ አገሪቱ ኢኮኖሚ ማደግ ይህ ነው የማይባል ውሸትና የተዛባ ሪፖርት ማቅረብ ከሆነ ሰንብቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት የዋጋ ግሽበቱ ከ40 በመቶ በላይ ሆኖ ሳለ እንኳን በየቀኑ የሚሰማው ፕሮፓጋንዳ ‹‹ኢኮኖሚያችን እያደገ ነው›› የሚል ቅጥፈት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ጠንክረን በመታገል ከወደቅንበት መከራና ስቃይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመገላለል፣ የህወሃት/ኢህአዴግን የአፈና ሰንሰለት በመበጣጠስ የሰላም ኑሮ የምንኖርበት ጊዜ እጅግ ማቅረብ እንችላለን።

አሁን በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለው መከራና ስቃይ እንዲሁም የአገዛዙ ለዚህን ሁሉ ዓመታት በሥልጣን ላይ መቆየት በምንም መልኩ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊፈጥር አይገባውም፡፡ ብዙዎቻችን ይህንን ሁሉ ስንመለከት በአገር ቤት ለውጥ ማምጣት ከባድ ነው በማለት እንድናስብ ልንገደድ እንችላለን። ሆኖ ግን እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ወደ ነፃነት የማያደርስ፣ የነፃነት ሰማዕታትን አሻራ የሚያደበዝዝ፣ ራስንና ልጅ ልጆችን ለባርነት አሳልፎ የሚሰጥ በመሆኑ ስህተት ነው። ይልቁንም ፈጣሪ የሰጠውን የሰው ልጅ ነጻነትና መብት ማምጣት የምንችለው እኛና እኛ ብቻ መሆናችንን በመረዳት በአንድነት ለነፃነታችን ልንነሳ ይገባናል። ራሱን ሰማዕት ያደረገው መምህር የኔሰው መልእክቱ እዚህ ላይ ነውና!! የሌሎች አገራት መንግስታት የእኛን ነጻነት ሊሰሩልን ወይም ሊፈጥሩልን አይችሉም። ነጻነት ከሌሎች አገራት እንደሚገኝ የምግብ እርዳታ እንካችሁ ተብሎ አይሰጥምና!! የኢትዮጵያ መጥፎ ገጽታ ለመለወጥ፣ ያደገችና የበለፀገች ኢትዮጵያ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ሁሉም ዜጋ የለውጥ ሃዋሪያ መሆኑን መረዳትና ማመን አለበት።

ታዲያ ለዚህ ጥሪ ደወል ምላሹ ዳግመኛ የሰው ሕይወት በማጥፋት መሆን የለበትም። ነገር ግን እንንቃ። የሕዝባችን የመከራና የሰቆቃ ሕይወት እንዲያበቃ በጋራ ሆነን ለነጻነት፣ ለፍትሕና ለሰው ልጅ ክብር ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥል። ከአቅማችን በላይ በሚሆንብን ነገር ሁሉ ደግሞ የፈጣሪ ድጋፍ ከላችን ጋር ይሁን። ለየኔሰው ቤተሰቦችና ወዳጆች በሙሉ ለደረሰባቸው መራራ ሃዘን መጽናናት፣ ብርታትና ጥንካሬን እንዲሰጣችሁ እንመኛለን።

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

